# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ - ወዛደር፣ ገበሬ፣ ነጋዴ፣ ወታደር፣ ምሁር -

መብትና ጥቅም የሚታገል ጋዜጣ

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ይቅደም

ቁጥር 35 ቀን 25/ 04/1968

## ለ "ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት" ወይንስ ለነቃ፣ ለተደራጀና ልታጠቀ የህዝብ ትግል

የየካቲት 1966 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦችን አብዮታዊ የትግል ትጥቅ ለማስፈታት ፊውዳሊስቶችና ኢምፔሪያሊስቶች እስካሁን ድረስ ያልገለበጡት ድንጋይ፣ ያልጠነሰሱት ሴራ የለም። እነዚህን ልዩ ልዩ ሴራዎችና ተንኮሎች እያከሸፈ፣ የጭቁኖች ትግል አገሪቱን ቢያጥለቀልቅም፣ አድሃሪ ሃይሎች የኢትዮጲያን ህዝብ ትጥቅ ለማስፈታት፣ ወይ ደግሞ እነሱ እያታለሉ በሁለተኛ ደረጃ በሚታዩ ጠላቶች ላይ በማስነሳት ትግሉን ለማዳከም፣ ተራማጆችን ለመከፋፈል፣ ከማሴር አልተቆጠቡም። ነገሩ የመደቦች ትግል ነውና ባገኙት ዘዴ ህዝቡን ለማዳከም፣ ትግሉን ለማቀዝቀዝ፣ ወይም የተሳሳተ አቅጣጫ ለመስጠት ቢሞክሩ አይገርመንም።

የኢትዮጵያ ጭቁኖች ትግል ግን የፊውዳሊስቶቹንና የነሲአይኤን ሴራ ተራ በተራ እያከሸፈ ይወጣቸዋል። ዞሮ ዞሮም በጠላቶቹ ላይ ሙሉ ድልን ይጎናፀፋል። በዚህ ትግል ውስጥም ፀረህዝብ ሃይሎች የተራማጅ ካባ ደርበው፣ እንዲያውም አልፈው ተርፈው በገናናዎቹ በነሌኒንና በነማርክስ ስም እየማሉና እየተገዘቱ፣ ለማወናበድ ይሞክሩ ይሆናል። ግን ሃቀኛ ማርክሲስቶች ደግሞ ሞልተዋል። ስለዚህ በአብዮት ስም አብዮቱን ለማጨናገፍ የሚመክሩ አወናባጆችም ትግሉ እየተፋፋመ ሲሄድ እየተጋለጡ እንደሚሄዱ ግልጽ ነው።

በኢትዮጵያ ተራማጆች መሃከል መከፋፈልን ለማጠንከር፣ የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች ዋና ጠላቶቻቸውን ችላ እያሉ ባልሆነ አቅጣጫ እንዲታገሉ፣ የድላቸውን ጎዳና እየተው በሌላ በማይገኝ አቋራጭ እንዲባክኑ፣ የጨለማው ዘመን እንዲራዘም የሚፍጨረጨሩ የንኡስ ከበርቴዎች ደንፊዎች ልሳን የሆነው ዲሞክራሲያ የሚነዛውን መርዝ መዋጋት አስፈላጊ ሆኖ ያገኘነው ለዚህ ነው። ፀረዲምክራቲኩምን የደርግ አገዛዝ እንደጊዜው ዋና ጠላት በመቁጠር የኢትዮጵያን ጭቁን ህዝቦች የደም እንባ ሲያስለቅሱአቸው የነበሩትንና አሁንም የሚያስለቅሱአቸውን ፊውዳሊስቶችና ኢምፔሪሊስቶች እኩል እንዲዋጉ የሚጋብዛቸውን የዚህን ጋዜጣ ቁጥር 23 <u>በሰፊው ህዝበ ድምጽ ቁጥር 33</u> ተችተንበት የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች ፀረዲሞክራቲኩን ደርግ እየተዋጉ፣ የሱንም ፀረዲምክራቲክ አገዛዝ እየታገሉ፣ አመዛኝ ጉልበታቸውንና ሃይላቸውን ዋና ጠላታቸው ላይ አንደሚያዉሉት፣ ማዋልም እንዳለባቸው አብራርተናል። ይህንን አዳሃሪ ጎራም እንደማንሰማ ገልፀናል።

በዚህ ቁጥራችን፣ እነዚህ በነማርክስና በነሌኒን ስም የተደባለቁንን ንኡስ ከበርቴ ደንፊዎች የኢትዮጳያ ጭቁን ህዝቦችን የትግል ትጥቅ ለማስፈታት እንደበግ ላት እንጠልጥለው የያዙትን የጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስታቸውን ጉዳይ አንስተን እንተቻለን። አደርባዮቹ የዲሞክራሲያ አዘጋጅዎች የልባቸውን በኤክስሬይ ተመክተን ተራማጅነታቸውን

ካላረጋገጥን በስተቀር በዚህ ጉዳይ ጨርሰው ከአስፈወሰን መንገሻ ስዩም፣ ከነሲአይኤ ጋር እንደተሰለፉ እናሳያለን፡፡ ከዚህም አልፈን እንሄዳለን፡፡ አድርባዮቹ ለዚህ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ጉዳይ አንድ ሙሉ ቁጥር አውለዋል፡፡ በዚህ ቁጥራቸው ላይ ሰልፋቸው ከፀረህዝብ ሃይሎች ጋር እንዳይደለ ለማሳየት በሩስያ አብዮት ጊዜ እነሌኒን የወሰዱት አቋም ልክ እንደኛው ነበር እያሉ ለርኩስ አላማቸው የገናናዎቹን ቦልፐሽቪኮች ስም ለመበከል ሞክረዋል፡፡ ስለዚህ እኛም ወደታሪክ ተመልሰን የነዚህን አድርባዮች የትንተና ችሎታ ዜሮነትና፣ የማወናበድ የማጭበርበር ሊቅነታቸውን ለአንባቢ እያሳየን እናጋልጣቸዋለን፡፡

ዛሬ በኢትዮጵያ ይህ የጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ጉዳይ ብዙ ሃቀኛ ተራማጆችን ያወናበደ ጉዳይ ነው፡፡ በዚያው ልክ ደግሞ አድሃሪ ተብሎ፣ ፀረህዝብ ተብሎ፣ አወናባጅ ተብሎ ምርጫ እንዲደረግና ፀረዲሞክራቲኩ ደርግ ተወግዶ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት እንዲቋቋም የማይጠይቅ የለም፡፡ ባለፈው ባህዳር ወር ከነአስፋወስን መንገሻ ስዩም በስተቀኝ አለሁ የምትል አንዲት ፀረደርግ ገስጋሽ ንቅናቄ ኢትዮጵያን ከጉግማንጉግ ለማዳን የተባለች የደንቆሮ ፊውዳሊስቶች ንቅናቄ በተነችው ወረቀት ላይ ጉግማንጉግ ደርግ ተወግዶ ህዝቡ በሚመርጣቸው ሲቪሎች እንዲተዳደር ትጠይቃለች፡፡ ይህ ጥያቄ ግን የሲ ብቻ አይደለም፡፡

አንድ የእድገት ደረጃ እንደተደረሰ፣ የቀድሞው ስርአት መዋቅር ፋይዳቢስነት ለሁሉም ግልጽ ይሆናል፡፡ ሁሉም አብዮት ይላል፡፡ በዚህ ጊዜ ያለው ተግባር ይህንን አዲሰ መዋቅር የትኞቹ መደቦች እንደሚገነቡትና እንዴት እንደሚገነቡት መግለጥ ነው፡፡ ይህ ካልተደረገ፣ አብዮት የሚለው መፈክር በአሁኑ ጊዜ ትርጉም አይኖረውም፡፡ /ሌኒን ቮል 9 ገጽ 128/

ዛሬም በአገራችን ይኸው ነው፡፡ የዚህን ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት የመደብ ይዘት በደንብ መግለጥ ያስፈልጋል፡፡ እንዴት እንደሚመጣም መግለጥ ያስፈልጋል፡፡ ይህ በትክክል ካልተደረገ፣ ማንም ተራማጅ ነኝ የሚል ሰው አውቆም ሆነ ሳያውቅ፣ ከአድሃሪዎች ጋር መሰለፉ ግልጽ ነው፡፡

በባሪያ ዘመን ህዝብ የሚለው ፈሊጥ የሚያመለክተው የባርያ ገዥዎችን መደብ ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ ለምሳሌ ግሪኮች ያቋቋሙ የነበረው ዲሞክራሲያዊ መንገስት ህዝባዊ ነኝ ቢልም የመምረጥና የመመረጥ መብት የነበራቸው ባርያ ገዥዎች ነበሩ፡፡ በፊውዳሉ ስርአት እነ አኤ ሃይለስላሴ ህዝብ ሲሉ የመሳፍንቱንና የባላባቱን መደብ አባሎች ለመጥቀም ነበር፡፡ ዛሬም እነአስፋወሰን ህዝባዊ መንግስት ሲሉ፣ እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ፣ የፊውዳሉን መደብ አባሎች ነው፡፡ በከበርቴ ስረአት ህዝባዊ መንግስት ሲባል ህዝብ ተብሎ የሚቆጠረው የከበርቴው መደብ ነው፡፡ በኢትዮጵያ በመካሄድ ላይ ባለው አዲሱ ዲሞክራቲክ አብዮት ደግሞ ህዝባዊ መንግስት ሲባል፣ ህዝብ የሚለው ክልል ውስጥ ወዝአደሩ አርሶበሌው፣ ንኡስ ከበርቴውና ሌሎችም ፀረፊውዳል ፀረኢምፔሪያሊስት የሆኑ ሃይሎች ሁሉ ይጠቃለላሉ፡፡ በተራማጅ ስም የሚፍሉ የዲሞክራሲያ አድርባዮች በያዝነው ዘመን እውነተኛው ህዝባዊ መንግስት የመደብ ይዘቱ እንዲህ መሆኑን አይስቱትም፡፡ ስለዚህ እነዚህ መደቦች ተደራጅተውና ታጥቀው

ጠላቶቻቸውን ሳይደመስሱ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ተመራረጠን እናቋቁማለን ሲሉ ለጊዜው የተደራጀው ንኡስ ከበርቴ መደብ ብቻውን ስልጣን ይያዝ ማለታቸው እንደሆነ ግልጽ ነው። በንኡስ ከበርቴ ደንፊዎች በኩል እንግዲህ ይህ መፈክር ሲወረወር ግፋ ቢል ንኡስ ከበርቴው ለጊዜው የኢትዮጵያ ህዝበ እኔ ልሁን ብሎ ለማቋቋም የሚታገለው የንኡስ ከበርቴ አምባገነንነት የሚፀድቅበት መንግስት ነው ማለት ነው። ይኸ ደግሞ ቢበዛ የጊዜያዊ ህዝብ መንግስት ይባል እንደሆነ እንጂ የአዲሱ ዲሞክራቲክ አብዮት ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት የሚባልበት ምንም ፈሊጥ የለም።

ስለዚህ የኢትዮጵያ ተራማጆች የሚታገሉለት ህዝባዊ መንግስት በመደብ ይዘቱ የሰፊው ህዝብ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ነው። በአመጣጡ ደግሞ፣ በዲሞክራሲያዊ ምርጫ ሳይሆን ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊስምን የሚደመስስ፣ የተደራጀና የታጠቀ ህዝብ አብዮታዊ አመጽን ይጠይቃል። የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች ተጋድሎ የሚወጣውን ፈተናና ችግር ተወጥቶ አልፎ የሚሄድበት ጎዳና፣ በአድሃሪ ሃይሎች ላይ ወሳኝ ድልን ተጎናጽፎ የሚጓዝበት ጎዳና ይህ ብቻ ነው።

ዛሬ በኢትዮጵያ ይምጣ የሚባለው መንግስት ህዝባዊ መንግስት እንደሆነ ፀረጎግማንጉን ገስጋሽ ንቅናቄ ትስማማለች። አስፋወሰን/መንገሻም ይስማማሉ፣ የነሲአይኤ ፍጡሮች የሆኑት እነ የኢትዮጵያ ዲምክራሲያዊ ህብረትም ይስማማሉ፣ እነዲሞክራሲያም ይስማማሉ። ሃቀኛ ተራማጆችም ትግላቸው ትንንቃቸው ለዚሁ ለህዝባዊ መንግስት ነው። ነገር ግን ሃቀኛ ተራማጆች ይህ ህዝባዊ መንግስት ሊመጣ የሚቻልበትን አብዮታዊ የትጥቅ ትግል ጎዳና ለጭቁኖች ሳይታክቱ እያሳዩ መራራ ትግላቸውን ያካሂዳሉ። ከፀረጉግማንጉን ንቅናቄ አንስተን ወደግራ እየተጓዝን እስከ ንኡስ ከበርቴ ደንፊዋ እስከዲምክራሲያ ድረስ ያለው የፀረህዝብና የፀረአብዮት ጥርቃሞ ደግሞ ለማወናበድና ሁሉም የበኩሉን የመደቡን ፀረህዝብ አምባገነን አገዛዝ ለማንገስ የሚሞክረው ይህንን አብዮታዊ ጎዳና እያጭበረበረ ነው።

ዛሬ ይህ የጊዜያዊ ህዝበዊ መንግስት መፈክር ይህንን አብዮታዊ የትግል ጎዳና ለማመላከት እስካልተገደዱ ድረስ የህዝቡን ትጥቅ ለማስፈታትና አብዮቱን ለመቀልበስ የሚዘጋጁ የጥፋት ሃይሎች ሁሉ የሚቀበሉትና የሚታገሉለት መፈክር ነው።

ሁሉም ይህንን መንግስት በዲሞክራሲያዊ ምርጫ እናመጣዋለን ይላሉ። ሁሉም የትግሉን መግፋት፣ የህዝቡን መደራጀትና መታጠቅ አጥብቀው ይፈራሉ። እነአስፋወሰን መንገሻ ስዩም ይህንን አፍረጥርጠው ይናገራሉ። የመንገሻ ስዩም የማርች 30 1974 መግለጫ ስልጣን ከምርጫ ሳጥን እንጂ ከጠመንጃ አፈሙዝ መውጣት የለበትም ያለው ይህንኑ የህዝቡን መታጠቅ የሚፈራ መደባዊ አቋሙን ሲያስተጋባ ነው። የዲምክራሲያ አድርባዮችም የትጥቁን ነገር ለማምለጥ የሚሞክሩት እሱን ችላ በማለትና የምርጫውን ነገር አጥብቀው በመያዝ ነው።

የነሲአይኤና የነአስፋወሰን የጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት መፈክር ሌላ አላማው ነገሩ አለቅጥ ሳይዘገይ ህዝቡ ትጥቁን ፈትቶ ወደምርጫ እንዲሄድ ለማድረግ የተጠነሰሰ ሴራ ነው። ህዝቡ በንቃቱ፣ በድርጅቱ፣ በትጥቁ

እየገፋ ከሄደና እነሱ ተደቁሰው ካለቁ በኃላ ምርጫ ቢደረግ እውነትም ህዝባዊ ምርጫ እንደሚሆን ያውቃሉ:: ስለዚህ አላማቸው ትግሉ ሳይገፋ ለማቀዝቀዝ ነው:: ይህ ትግሉ ይብረድ የሚለው ቅዠታቸው ራሱ ለመንግስታቸው በሚሰጡት ስም ላይ ተለጥፎ ያጋልጣቸዋል:: የመንገሻ ስዩም የማርች 30 መግለጫ ይህንን ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስቱን የብሄራዊ እርቅና የሃገር መገንባት ዲሞክራሲያ አድርባይ ምሁራንም በወፍ ቋንቋ አድበስብሰው ያቅርቡት እንጂ ከአቀራረባቸው የህዝቡ ትግል እንኳን መታጠቁን ይቅርና በወጉ ስር ሰድዶ መደራጀቱን ይፈራሉ:: በምርጫ ተውጣጥቶ ይቋም የሚለት ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት የሚውጣጣው አሁን ካሉት፣ ከፈረሱትና፣ ባጭር ጊዜ ውስጥ ሊቋቋሙ ከሚችሉት ህዝባዊ ድርጅቶችና ... ፓርቲዎች ነው ብለው እንመራረጥ ነው የሚሉት:: እንዲያውም እስቲ ወደዚህ ወደጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስታቸው አመጣጥ ጉዳይ ጠለቅ ብለን እንግባ::

መጀመሪያ ነገር የአድርባዮቹ ውዥንብር የሚጀምረው ገና ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስቱ የሚለው ቃል ላይ ነው:: እነሌኒን ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግስት ሲሉና አድርባዮቹ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ሲሉ በአብዮትና በፀረአብዮት፣ በብርሃንና በጨለማ፣ በጥራትና በውዥንብር መሃከል ያለው ልዩነት እንዳለ መመልከት ያስፈልጋል:: ህዝባዊ መንግስት የሚባለው መላው ህዝብ ተሳትፎበት ከተካሄደ ነፃ፣ ምስጢርና ቀጥታ ከሆነ ጠቅላላ ምርጫ የሚወጣ መንግስት ለማለት ነው:: የሚገዛውም በፀደቁ፣ ባሉ፣ ሁሉ በሚያውቃቸው ህጋጋትና የስልጣን ክፍፍሎች ላይ የተመረኮዘ የተረጋጋ መንግስት ለመጠቆም ነው:: አብዮታዊ መንግስት ግን በጠቅላላ ምርጫ ሳይሆን፣ በአብዮታዊ ትግል በደመሰሰው መንግስት ተተክቶ፣ በቆዩና በተደነገጉ በተረጋጉ ህጋጋትና የስልጣን ክፍፍሎች ላይ ሳይሆን ለትግሉ መግፋትና ለፀረአብዮት ሃይሎች መደምሰስ አስፈላጊ የሆኑትን እርምጃዎች ሁሉ እየወሰደ፣ አዲስ ስርአት መልክ ባለው ሁኔታ እስካቋቋመ ድረስ የሚሰራ የመሸጋገሪያ መንግስት ነው:: እንዲህ አይነቱ ስልጣን በአብዮቱ አፍላ ጊዜ የሚቋቋምና በሌኒን አነጋገር ምን ሌላ ስልጣን የማያውቅ፣ ያወጣ ባለስልጣን ቢያወጣቸው ምንም ህጋጋት፣ ምንም ደንቦችና ወጎች የማያዙት፣ ወሰን የሌለው፣ ከህግ ውጭ የሆነና በቀጥታ በሃይል ላይ የተመሰረተ መንግስት ማለት ነው::

እንዲያውም እነሌኒን እንዲሃ አይነቱን ጊዜያዊ አበዮታዊ መንግስት የጠየቁት ዝቅ ብለን እንደምናየው፣ አንዱ አለማው ጠቅላላ ምርጫው በመላው ህዝብ፣ በቀጥታ፣ በሙለ ነፃነትና በምስጢር ለማስደረግና ህዝባዊ ሪፑብሊክን የሚያቋቁም ባለሙሉ ስልጣን የእንደራሴዎች ሸንጎ ለማስመረጥ ነው:: በነሌኒን እምነት ይህ ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግስት ሊቋቋምና ነፃ ምርጫውን ሊያካሂድ የሚችለው በፀረህዝበ ሃይሎች ላይ የተሳካ ህዝባዊ አመጽ አድርጎ ስልጣን ሲጨብጥ ብቻ ነው:: ጀግኖቹ የቪየትናም አርበኞችም በትግል ውስጥ ባሉበት ጊዜ ብዙ ግዛቶችን ከቁጥጥራቸው ስር ካደረጉ በኃላ በምርጫ ሳይሆን በአብዮታዊ አመፃቸው ላይ ተመርኩዘው ያቋቋሙት መንግስት ጊዜያዊ አብዮታዊ እንጂ ጊዜያዊ ህዝባዊ ያልተባለው ለዚህ ነው::

እንግዲህ አንድ ህዝባዊ መንግስት ጊዜያዊ ይባል ቋሚ ከመላው ህዝብ ምርጫ የሚፈልቅ መንግስት ነው:: አብዮቱ ተሳክቶ ፀረህዝብ ሃይሎች ተደምስሰው፣ ወይም ከቁጥጥር ስር ውለው ነፃ ምርጫ ተደረገ እንበል:: ይህ ከሆነ ከዚህ ነፃ ምረጫ የሚወጣው መንግስት በርግጥም ህዝባዊ የሆነ መንግስት ለምን ጊዜያዊ እንደሚባል ጨርሶ ምስጢረስላሴ ይሆንብናል:: በሌላ በኩል ደግሞ ፀረአብዮት ሃይሎች አይለው ህዝቡ በሙሉ ነፃነት ምርጫውን እንዲያካሂድ ከከለከሉት፣ ወይም አድሃሪ ተጽእኖዋቸውን ካሳደሩበት ይህ ጊዜያዊ ጉድ በምን ፈሊጥ ህዝባዊ ሊባል እንደሚችል አሁንም ከምስጢረስላሴ የረቀቀ ምስጢር ይሆንብናል:: ባጭሩ አድርባዮቹ እናመጣዋለን የሚሉት መንግስት በርግጥ ህዝባዊ ከሆነ ጊዜያዊ መሆኑ አይታየንም:: ህዝባዊ ካልሆነ ደግሞ የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች በትግላቸው ገፍተው ነፃ ይወጣሉ እንጂ ለጊዜውም ቢሆን የምትጭኑባቸውን ባርነት አይቀበሉም:: ጊዜያዊ እና ህዝባዊ አንድ ላይ የሚሄዱ ነገሮች አይደሉም:: እሳትና ጭድ ናቸው:: ብቻ ገና ስንት የተደገሰለትን አንባቢ በእንደዚህ አይነቱ ፀጉር መሰንጠቅ እናድክመውና ወደሌላ እንቀጥል::

የዲሞክራሲያ አዘጋጅዎች በዚህ ጉዳይ ላይ ከነአስፋወሰንና ከነመንገሻ ስዩም ጋር ቆመው ሲያራግቡ የሚያዙት ስለዚህ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስታቸው መተቸት ሲጀምሩ ነው:: በነሱ ግምት የዚህ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት አመጣጥና ቅደም ተከተል እንደሚከተለው ነው::

- ለህቀኛ አብዮታውያን የትግል መሳሪያ የሆኑት የመሰብሰብ፣ የመናገር፣ የመፃፍ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግና የመደራጀት ሰብአዊ መብቶች ያለምንም ገደብ መልቀቅ፣

- አሁን ካሉት የፈረሱትና በአጭር ጊዜ ለመቋቋም ከሚችሉት ህዝባዊ ድርጅቶችና የገበሬ ማህበራት፣ የንኡስ ከበርቴ የሙያ ማህበራት፣ የሴቶች ማህበራት፣ የሰራተኛ ማህበራት፣ የመምህራን ማህበራት፣ ሰፊው ወታደር../ ፓርቲዎች በምርጫ የሚውጣጣ ጊዜያዊ ህዝባዊ ሸንጎ ማቋቋም፣

- በዚህም ጊዜያዊ ህዝባዊ ሸንጎ የሚመረጥ ጊዜያዊ መንግስት መመስረት ያስፈልጋል::

ለምን እንደዚህ በኢትዮጲያ ጭቁን ህዝቦች አንባና መከራ ታላግጣላችሁ? አሁን ማን ይሙት የኢትዮጵያ ጭቁኖች በነፃ ስለተናገሩ፣ ሰላማዊ ሰልፍ ስላደረጉ ... ብቻ ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም በንግግርና በሰላማዊ ሰልፍ ብርታት ተንኮታኩተው ይወድቁ መስሎአቸው ይሆን? የኢትዮጵያን ህዝቦች ጥያቄ በዚህ ብቻ እስከወሰናችሁት ድረስ እነሲአይኤም አብረዋችሁ ይሰለፋሉ:: ይህንንማ እነአስፋወሰን መንገሻም አስከነስሙ የኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ህብረት ብለው በሰየሙት ድርጅታቸው ፕሮግራም ላይ በሙሉ ለኢትዮጵያ ህዝብ ጠይቀውታል:: ነገር ግን የኢትዮጵያ ጭቁኖች በነዚህ መብቶች ላይ በተጨማሪ፣ የነአስፋወሰን መንገሻን፣ የኢምፔሪያሊስቶችን አመጽ ለመመከት፣ በገዛ አገራቸው በሰላም ለመስራትና ለመኖር እንዳይችሉ ከታወጀባቸው የርስ በርስ ጦርነት በድል

አድራጊነት ለመውጣት የመታጠቅ መብታቸውን ይጠይቃሉ። ይህማ ከሌለ ያየነው ነው። ሚልዮን የመጋር መብት ቢኖራቸው፣ ባዶ እጃቸውን እስከሆኑ ድረስ የታጠቀ አድሃሪ አያናግራቸውም። ሚልዮን የመደራጀት መብት ቢታወቅላቸው የታጠቀ አድሃሪ ይበትናቸዋል። ዛሬ አብዮታዊ ዘማቾች በጥይት እየተቆሉ፣ በእሳት እየተጠበሱ መስዋእትነትን ተጋፍጠው በመጋገል ላይ ናቸው። ይህ ሁሉ የሚወርድባቸው የአድሃሪዎች አመጽ እስከዚህም የመደራጀት መብት በመነፈጉ ሳይሆን በፀረዲምክራቲኩ የደርግ አገዛዝ የመታጠቅ መብቱን በመንፈጉ ነው። ይህ አላገባችሁ እንደሆነ ስለኢትዮጵያ አብዮት የገባችሁ ሳንቲም ነገር የለም ማለት ነው።

አድርባዮቹ የጭቁን ህዝቦችን መታጠቅ በጣም ይፈራሉ። ስለዚህ ይህንን ሳያነሱ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስታቸው እንዴት ሊቋቋም እንደሚችል ለመጠቆም ሲሞክሩ ጨርሰው ትርምስ ውስጥ ነው የሚገቡት።

በመጀመሪያ ነገር ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስታቸውን ከነሌኒን ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግስት ጋር የግድ ለማዛመድ ቢሞክሩም የአድርባዮቹ መንግስት አቋቋም ቅደም ተከተል ሲታይ ከአብዮታዊ ጊዜያዊ መንግስት ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለው ግልጽ ይሆናል። እንደዲሞክራሲያ አባባል ከሆነ በመጀመሪያ ጊዜያዊ ህዝባዊ ሸነን ከምርጫ ይውጣጣና ከዚያ በኋላ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ይመረጣል። በጣም ጥሩ የነሌኒን ደግሞ የተገላቢጦሽ ነው የእነሱ ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግስት ከምርጫ ተውጣጥቶ ሳይሆን ከተሳካ ህዝባዊ አመጽ ይወለዳል። ከዚያ በኃላ ጠቅላላው ህዝብ ነፃ፣ ቀጥታና ምስጢር በሆነ ምርጫ ተሳትፎ ህዝባዊ የመማክርት ሸንጎ ያቋቁማል። ይህ ባለሙሉ ስልጣን የሆነ የህዝብ እንደራሴዎች ሸንጎ ህዝባዊ መንግስት ያቋቁማል።

የትጥቅን ነገር ፈጽሞ አረሳስታችሁ፣ በምርጫ እናመጣዋለን የምትሉት መንግስት እንኳን ከነሌኒን አብዮታዊ መንግስት ጋር አንድ ሊሆን ይቅርና የሱ ተቃራኒ እንደሆነ ግልጽ ነው። አድርባዮቹ ግን ይህን አድሃሪ መፈክራቸውን በገናናዎቹ በነሌኒን ስም ሸፋፍነው ለማሳለፍ የጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስትን ጠቃሚነት የሚያረጋግጡ ታሪካዊ ሃቆች አሉን /?/ በሚል አርእስት ስር የፉስያን ቦልሺቪኮች ታሪክ ምሳሌነት እየጠሩ ይተነትናሉ። የዲሞክራዊያን ቁጥር 24 ይህንን የመጨረሻ ክፍል ስናይ ለኢትዮጵያ ተራማጆች ገና ለረጅም ጊዜ ሲያሳፍረን የሚኖረውን የክርክርና የአጠቃቀስ ዘዴ ታዝበን አዘንን። ይህንን ዝቅ ብለን እንመጣበታለን።

በዚህ በጊዜያዊ አበዮታዊ መንግስት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን በቦልዚቪኮችና በሜንሼቪኮች መሃከል ብዙ ሌሎች ልዩነቶች ነበሩ። በጠቅላላው ግን የልዩነታቸው መሰረት እነሌኒንና አድርባዮቹ ስለጠቅላላው የሩስያ አብዮት የተለያየ አስተሳሰብ ስለነበራቸው ነው። በ1905 ዓ.ም. የንጉሱ አገዛዝ በህዝብ ትግል ተወጥሮ ተይዞ ሳለ እየተጋጋለ የሚሄደው አብዮት እንዴት እንደሚጋፋ በተደረገው ውይይት ሁለቱ ቡድኖች የተለያየ ታክቲክ ለመከተል ወሰኑ።

እነሌኒን ይህ አብዮት፣ ምንም እንኳን የከበርቴ አብዮት ቢሆን ቅሉ፣ ከበርቴው እጅግ ወላዋይ በመሆኑ ከንጉሱ ጋር ተዋውሎ አንድ አይነት ቅይጥ መንግስት ያመጣ እንደሆን እንጂ፣ በእርግጥ ዲምክራሲያዊ ሬፑብሊክን ሊያመጣ አይችልም፡፡ ይህንን ዲሞክራሲያዊ ሬፑብሊክ ለማምጣት የሚችለው ወዝአደሩ ከአርሶአደሩ ጋር ተባብሮ ፈላጭ ቆርጭ የሆነ ዲምክራሲያዊ የወእአደርና የገበሬ መንግስት ለመመስረት በመሪነት ሲታገል ነው እያሉ ይከራከሩ ነበር፡፡ ይህንንም የወዝአደርና አርሶአደር አምባገነን መንግስት፣ ይህንን ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ለማቋቋም አንድ ባለሙሉ ስልጣን የሆነ የህዝብ እንደራሴዎች ሸንጎ ማስመረጥ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ሸንጎ በርግጥ ባለሙያ ስልጣን እንዲሆን፣ በርግጥ የህዝበ እንደራሴዎቸ ሸንጎ እንዲሆን ከተፈለገ ይህንን ምርጫ ሊያካሂድ የሚችለው <u>በተሳካ ህዝባዊ አመጽ አድሣሪዎችን ደምስሶ የሚቋቋም ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግስት ብቻ እንደሆነ</u> እነሌኒን ደግመው ደጋግመው ያስረዱ ነበር፡፡

አድርባዮቹ ሜንፔቪኮችስ? ሜንሼቪኮች ይህ አበዮት የከበርቴ አብዮት እንደመሆኑ መጠን ሊመራው የሚችለው ለዘብተኛው /ሊበራሉ/ ከበርቴ እንጂ ወዝአደሩ እመራለሁ ብሎ ከበርቴውን ማስደንገጥ የለበትም ይሉ ነበር፡፡ ከዚህም አልፎ ተርፎ ወዝአደሩ ከገበሬው ጋር አንድነቱን ማጠንከሩን ትቶ ትብብሩን ከዚህ ከለዘብተኛው ከበርቴ ጋር ያድርግና ንጉሱን ለመጣል በሚያደርገው ትግል ይርዳው ይሉ ነበር፡፡ ከበርቴው ተደናግጦ አብዮቱን እንዳይተወው ወዝአደሩ የዚህን መንግስት እንኳን አመራሩን ይቅርና ተሳትፎ እንኳን መጠየቅ የለበትም የሚል አቋም ነበራቸው፡፡ የንጉሱን አገዛዝም ለመደምሰስ እንግዲህ እነሌኒን የትጥቅ ትግልና እሱ ሲሳካ ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግስት፣ ከዚያም ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ሲሉ አድርባዮቹ ወይ የተሳካ ህዝባዊ አመጽ ተደርጎ ወይም ደገሞ ህዝቡ የእንደራሴዎች ሸንጎ እንዲጠራ አስጨንቆ ይዞ ምርጫ እንዲደረግ ቢያስወስን ወሳኝ የሆነ ድል /ዲሳይሲብ ቪክትሪ/ ይገኛል ብለው ይቃዡ ነበር፡፡

ሌኒን ይህ ድል ሊገኝ የሚችለው ከተሳካ ህዝባዊ አመጽ ብቻ ሊወጣ በሚችለው ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግስት ብቻ እንደሆነና ፀረህዝብ ሃይሎች ሳይደመሰሱ ወይም ሳይዳከሙ ምርጫ ቢደረግ በምንም አይነት እንደድል ሊቆጠር እንደማይቻል ሲያስረዳ የሶስተኛውን የፓርቲውን ጉባኤ ውሳኔ እየተቸ እንዲህ ይላል፡፡

የጉባኤው ውሳኔ እንደሚያመክትው የቅስቀሳ ሙሉ ነፃነትን አረጋግጦ፣ በእውነት የህዝቡን ፍላጎት ለማንፀባረቅ የሚችል ባለሙሉ ስልጣን የእንደራሴዎች ሸንጎ ለማስመረጥ የሚችለው፣ የተሳካ ህዝባዊ አመጽ መሳሪያ የሆነው ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግስት ብቻ ነው፡፡ ይህ አስተሳሰብ ትክክል ነው ወይ? እቃወማለሁ የሚል ካለ የንጉሱ መንግስት ለአድሣሪዎች እጁን ላይዘረጋ ይችላል፣ በምርጫው ውስጥ ገልልተኛ መሆን ይችላል፣ ህዝቡ በእውነት ፍላጎቱን እንዲገልጽ ይፈልጋል ብሎ መከራከር ይኖርበታል፡፡ እነዚህ አስተሳሰቦች እጅግ አስቂኝ ከመሆናቸው የተነሳ /አድርባዮች አዳምጡት ሌኒንን ስህድ / ማንም ቢሆን በግልጽ ሊቆምላቸው አይችልም፡፡

በነገራችን ላይ አድርባዮቹ /የኛን ማለታችን ነው/ ይህ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስታቸው ምን አይነት ድል እንደሆነ ራሳቸው እርግጠኞች አይደሉም። ስለዚህ መንግስት ምንነት ብዙ ከተናገሩ በኃላ ገጽ 5 ላይ ይህ የፊውዳሊስቶቹና የነሲአይኤ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት በምርጫ ተውጣጥቶ ቢቋቋምም የተገኘው የውሸት ድል ፀረህዝብ ድል እንጂ ሌላ ምንም ነገር እንዳይደለ ሲያምኑልን ይህ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ወደሃቀኛ ህዝባዊ ድልም የሚመራ የትግል መሳሪያም ነው ብለውን ቁጭ ይላሉ። ብቻ ይህንን እንተወውና ወደሌላው ትንተናቸው ገብተን እንዳክር።

እንግዲህ የነሌኒንና የሜንሼቪኮች ልዩነት ባጭሩ በነዚህ ነጥቦች ላይ ነበር። ከላይ ስንጽፍ በዚህ ጉዳይ ላይ የኛ አድርባዮች እነሌኒንም እንደኛው በምርጫ የተውጣጣ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ነበር የሚጠይቁት፣ እኛ በተነሳው ክርክር በቦልሼቪኮች በኩል ነበርን፣ ታሪክ ይደግፈናል ለማለት ያቀረቡትን ጥቅስና የሰሩትን ማጭበርበር ስናይ ለኢትዮጵያ ተራማጆች አፈርን ብለነው ነበር። ለአንባቢም ጉዱን እናሳየውና ሃፍረት አይሰማው እንዲሁ እንይ።

ስለአብዮታዊ አመጽ፣ ስለሚቋቋመው የመንግስት አይነት /የመደብ ይዘት/፣ ስለነበሩት ልዩነቶች ሳንቲም ሳያወሩ፣ ቃል ሳይተነፍሱ በ መንግስት ቦታ ስለሚቋቋመው/?/ ጊዜያዊ አበዮታዊ መንግስት ላብአደሩም ስለሚኖረው ተሳትፎ ማርክሲስቶቹ ቦልሼቪኮችና አድርባዮቹ ሜንሼቪኮች የተለያዩ አቋሞች ወስደው ነበር ይሉናል። እንኳን የልዩነቱን ታሪክ በሚገባ የሚያውቅ ሰው ይቅርና ከላይ የሰጠነውን ትንተና የተመለከተ አንባቢ እንዴት በዚህ ብቻ ነው ልዩነቱ? ብሎ መገረም ይገምራል። ከዚያ የቦልሼቪኮቹ መሪ የነበረው ሌኒን፣ ሁኔታውን እንደሚቀጥለው በመመልከት ይሉና ሌኒንን የጠቀሱ መስለው እንደሚከተለው ይጽፋሉ።

> ... የሚቋቋመው ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግስት ተግባር የአብዮቱን ድል ማጠናከር፣ ፀረአብዮታዊ እንቅስቃሴውን መደምሰስና የሶሻል ዲሞክራቲኩን ሌበር ፓርቲ ዝቅተኛ ፕሮግራም በስራ ላይ ማዋል ይሆናል። እነዚህ ተግባራት ካልተከነወኑ በስተቀር በዛሩ ላይ የተሟላ ድል ሊገኝ አይችልም። እነዚህን ተግባራት በስራ ለማዋልና በዛሬ ላይ ሙሉ ድል ለመቀዳጀት ደግሞ ጊዜያዊው አብዮታዊ መንግስት እንደማንኛውም ተራ አይነት ፣መንግስት ሳይሆን የላብአደሩና የአፈርገሬው አምባገነን መንግስት መሆን አለበት። ... ላብአደሩ በጊዜያዊው አብዮታዊ መንግስት ተሳትፎ አብዮቱን መምራት አለበት። እ...

አንድ የመጀመሪያ ነገር፡ ፡ እዚህ ላይ አድርባዮቹ ሌኒንን አሳይተው የሚጠቅሱት ስታሊንን ነው። ሌኒን እነዚህን አሳቦች አልሰነዘረም ለማለት አይደለም እዚህ ላይ ፀጉር እንሰንጥቅ የምንለው። አድርባዮቹ ነገሩ እንዲህ በመኀማመዱ አንባቢ ድንገት ግራ ተግቶ እስኪ ላጣራ ቢል እንዳይጋለጡ አስበው ነው ይህንን የጠቀሱት ከስታሊን ሂስትሪ ኦፍ ዘ ኮሙኒስት ፓርቲ ኦፍ ዘ ሶቪየት ዩኒየን ከተባለው መጽሃፍ ገጽ 64 እንደሆነ የሸሸጉን። ይብላን ለአወናባጆች እኛስ ደረስንነበት።

የነሌኒንን ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግስት አድርባዮቹ እናቋቁም ከሚሉት፣ በምርጫ አውጣጥተን እናምጣ ከሚሉት መንግስት ጋር አንድ ለማስመስል የሚቻልበት ጥቅስ አይደለም፡፡ የነሌኒንን የነስታሊንን አስተሳሰብ አረፍተ ነገሮችን እየጎመዱ ለማጣመም ካልተሞከረ በስተቀር ቃላትን ሳይቀር ከጀመሩ በኃላ እየተደናገጡ እርግፍ አድርጎ ካልተተወ በስተቀር፡፡ የጠቀሱት ጥቅስ ላይ የሚቋቋመው ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግስት ከሚለው አረፍተነገር በፊት ሌላ የሸሸጉን አረፍተነገር አለ፡፡ እሱውም የሚለው እንደሚከተለው ነው፡፡

> ሌኒን ከተሳካ ህዝበዊ አመጽ በኃላ የዛሩ መንገስት በጊዜያዊ አብዮታዊ መንግስት መተካት አለበት እያለ ይከራከር ነበር፡፡ የሚቋቋመው ጊዜያዊ አበዮታዊ መንግስት እያለ ነው ስታሊምን የሚቀጥለው፡፡ ከዚያ አድርባዮቹ ይህ መንግስት የላብአደሩና የአፈር ገፊው አምባገነን መንግስት መሆን አለበት ብለው አረፍተነገሩ ሳያልቅ ጨለማ ውስጥ ጥለው ሲለዩን ስታሊን የወዝአደሩና የአርሶአደሩ አብዮታዊ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ መሆን አለበት ብሎ እቅጩን ይነግረናል፡፡

አድርባዮቹ ከዚህ አልፈው ወደተሳትፎ ጥቅሳቸው የሚሄዱት ገጽ ዘለው ነው፡፡ ግን ስታሊን ስለዚህ መንግስት አምባገነነንነትና አብዮታዊነት ምን አውርቶ ነው አወናባጆቹ ነጥብ ነጥብ አድርገው ያለፉት? ያቺ እ... ብለው የጀመሯት ቃል ምን ትሆን? ይቺን ለመረዳትና አንባቢ በነዚህ አድርባዮች አንጀቱ እንዲቆርጥ ስታሊን ከዚህ አከታትሎ የዚህን በዛሩ ላይ የሚገኝ የተሟል ድል ይዘት የዚህን ጊዜያዊ መንግስት አብዮታዊነት ለማስረዳት ሌኒንን ይጠቅሰውና ይህ አድርባዮቹ ሊያዘልሉን የፈለጉትን ከጦር የሚፈሩትን የትጥቅ ጉዳይ ቁልጭ አድርጎ ያመጣላቸውና ጨርሶ ያጋልጣቸዋል፡፡ በኛ ግምት እ ብለው የጀመሯት ተጎርዳ የቀረችው ጥቅስ እነሆ፡

> እንደዚህ አይነቱ ድል ደግሞ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ እንጂ ሌላ አይደለም፡፡ ይህም ማለት የግድ በጦር ሃይል ላይ፣ በሰፊው ህዝብ መታጠቅ ላይ የሚመረኮዝ አገዛዝ እንጂ በዚህ ወይም በዚያ አይነት በህግ በታወቁ በሰላማዊ መንገድ በተቋቋሙ ድርጅቶች /ኢንስቲቱሽንስ/ ላይ የሚመረኮዝ አገዛዝ አይደለም፡፡ የግድ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ መሆን አለበት፡፡ ምክንያቱም ለወዝአደሩ፣ ለአርሶአደሩ በአስቸኳይና በግድ የሚያስፈልጓቸው ለውጦች የመሬት ከበርተዎች የከፍተኛ ቡርዥዋ መደብና የንጉሳዊው አገዛዝ ተቃውሞ ያጋጥማቸዋል፡፡

ግልጽ ነው፡፡ ወንድሞቻችን የቆሙላት ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት እነሱ እንደሚሉት በታሪካዊ ሃቅ አልተደገፈችም፡፡ ታሪካዊ ሃቅ የሚመሰክረው ጉዳይ ቢኖር 1ኛ/ ወንድሞቻችን ከቦልቬቪኮች ጋር እንዳልሆኑ፣ 2ኛ/ ማንቬቪኮች እንኳን ከአቅማቸው አጥብቀው አይያዙት

እንጂ የትጥቁን ጉዳይ አልፎ አልፎ ጠይቀዋል።  ግን ድል የሚገኘው ወይ በትጥቅ ትግል ወይ በምርጫ በማለው ፈሊጣቸው በወዝአደሩ ህሊና ውዥንብር ይነዛሉ ብሎ ሌኒን ተቃውሟቸው ነበር።  በዲምክራሲያ አስተሳሰብ ግን ምንም ውዥንብር የለም።  የድል ጎዳና ብላችሁ የምታሳዩት የቅድመ አብዮት ሩስያ ለዘብተኛ ከበርቴን የምርጫ መንገድ ብቻ፣ የነአስፋወሰን /መንገሻን የምርጫ መንገድ ብቻ ስለሆነ አስተሳሰባችሁ አድሃሪ ጥራት አለው።  እንደዚህም በመሆኑ የዲሞክራሲያ አዘጋጅዎች ሚልዮን ጊዜ ተንጠራሩ እንጂ አሰላለፋችሁ እንኳን ከቦልሼቪኮች ጋር ሊሆን ይቅርና ከሩስያ ሜንሼቪኮች በስተቀኝ እንደነበረና በዚያን ጊዜ እንደእናንተው የትጥቁን ጉዳይ ሳያነሱ ምርጫ ይደረግ ከሚሉት ከሩስያ መሳፍንት ግን እንደሆነ ግልጽ ነው።

የለም ቆይ የኛ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ከምርጫ የተውጣጣ ነው አልን እንጂ የነአስፋወሰን መንገሻ መንግስት አይደለም።  እንዲያውም እነሱን የሚቃወምና እነሱም የሚቃወሙት መንግስት ነው እያሉ አድርባዮቹ ከወንበራቸው ብድግ ሲሉ ይታየናል።  መውጫ ቀዳዳ የተገኘ መስሎአቸው ይቺው ዲምክራሲያ ቁጥር 24 የጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ተቃዋሚዎች እነማን ናቸው በሚል የተቸችውን ጠቁመው ለማምለጥ ይሞክራሉ።  እውነትም ለጠላት ስም የሚሰጠውን ዝርዝር የተመለከተና፣ ያስጨበጡትን የምርጫ ተስፋ የሙጥኝ ብሎ ያነቀ የዋህ ይህንን ሊስት ሊመለከት ጨርሶ ሊደናገጥ ይችላል።  አብዮታውያን ግን ይህንን ሊስት ሊመለከቱ የዲምክራሲያን አዘጋጅዎችና የጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስታቸውን ማንነትና በሊበራል ከበርቴ ቅዠት ተውጦ የሚዋዥቀውን የፖለቲካ መስመራቸውን ኪሳራ ጥልቀት ከመቼውም ይበልጥ ይረዳና ይቆርጥላቸዋል።  እንደዲምክራሲያ አባባል፡

የዚህ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ተቃዋሚዎች እነማን ናቸው

በመጀመሪያ ደረጃ፣ ስልጣን የጠማውና በህዝቡ ብሶትና ጭንቀት ተንሰራፍቶ ለመቆየት የሚፍጨረጨረው የምርጥ መኮንኖች መንግስት የዚህ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት አይነተኛ ተቃዋሚ ነው።

በየቦታው ህዝቡን እያወናበዱ እንደገና የፊውዳሉ ስርአት ትንሳኤ እንዲያደርግ የሚጥሩት መሳፍንቶችና ባላባቶችም የጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ተፃራሪዎች ናቸው።

የህዝባዊ መንግስት መቋቋም የብዝበዛ ግምታቸውን የሚሰባብርባቸው የነቢሮ ከበርቴዎችና አቀባባይ ከበርቴዎች የጊዜያዊ ህዝባዊውን መንግስት መቋቋም ለማክሸፍ አይመለሱም።

በተራማጅ ለምድ ተሸፋፍነው የህዝቡን አብዮታዊ የትግል ግለት ለማቀዝቀዝና አቅጣጫውን ለማስቀየት የሚቅበዘበዙት ሶቫልቮቪኒስቶችና ሶቫልፋሽስቶች ሌሎችም የጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ጽኑ ተቃዋሚዎች ናቸው።

የሃገሪቱን የሰው ጉልበትና ጥሬ ሃብት በርካሽ ዋጋ እያንጋፈፉ በሌላ በኩል የፋብሪካዎቻቸውን ግስንግስ በእጥፍ ድርብ ዋጋ እያራገፉ ህዝቡን

የሚበዘብዙትና የሚያልቡት አለምአቀፍ ባለወረቶች ዲሞክራሲያዊው ህዝባዊ መንግስት እነዚህን የትርፍ ትርፍ ምንጮቻቸውን ስለሚደፍንባቸው መቋቋሙን አጥብቀው ይቃወማሉ። ከስልጣን ላይ ካለው የምርጥ መኮንኖች አቀባባይ ከበርቴዎችም ጋር በመመሳጠር ልዩ ልዩ ወጥመዶቾ ይዘረጋሉ።

ማስኪን ዲሞክራሲያ ያኔ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ተቃዋሚው ብዙ ነው ብላ ጠላቶችዋን እንደአሸዋ እየቆለለች ስትደነፋ፣ በዚህ ብቻ ይህ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት <u>አብዮታውያን እንደሚሉት</u> በታጠቀ ህዝባዊ አመጽ እንጂ እሷ እንደምትለው ከምርጫ በማውጣጣት ለማቋቋም እንደማይቻል ወለል አድርጋ አምናልን ራሷን በጥፊ መታችና ቁጭ አለች።

እዚህ ላይ መቼስ ቢያንስ ቢያንስ ተራ ሊበራል ከበርቴ እንደሆናችሁ ብታምኑልን ይሻላችኋል። አለበለዚያ የባሰ ጉድ ነው።

መቼም አንድ ሰው አድርባይም ሆኖ ተራ ሎጂክ ሊገባው ይችላልና እናንተም የሚከተለውን ልብ እንድትሉ እንጠይቃችሃለን። ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስታችን እነዚህ ሁሉ ጠላቶች አሉበት ስትሉ አይነተኛ ተቃዋሚው ጽኑ ተቃዋሚው የዚህን መንግስት መቋቋም ለማክሸፍ የማይመለሰው ተፃራሪው አልፎ ተርፎም ይህ ሁሉ የፀረህዝበ ጥርቅም እየተመሰጠረ ልዩ ልዩ መጥመዶችን እየዘረጋ ያስቸግራል ስትሉ ይህንን መንግስት ለማቋቋም ሃይለኛ ተጋድሎ እንደሚያስፈልግ ታምናላችሁ ማለት ነው። ይህን ሁሉ ተቃውሞ ማሸነፍ አለበት ማለት ነው። ለዚህም የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች የረዥም ጊዜ የተወሳሰበ ፖለቲካና የጦር ትግል አያስፈልጋቸውም ትሉ እንደሆነ፣ በምርጫ በመውጣታችን ብቻ ተደናግጠው ኢትዮጲያ ህዝቦች ጠላቶች ከታሪክ መድረክ ይወርዳሉ ትሉ እንደሆነ መቼስ ከሊበራል ከበርቴ ቅዠታችሁ አንድትነቁ መፀለይ ሌላ የምናደርግላችሁ ነገር የለም። ግን ከፍ ብለን እንዳልነው ይህንን ብታምኑልን ይሻላል። አለበለዚያማ አላማችን ከነዚህ እንመራረጥ ከሚሉ ፊውዳሊስቶችና አቀባባዮች ሁሉ ጋር ሆነን፣ ፀረደርግ የሆነ ዲሞክራሲያዊ መንግስት ለማቋቋም ነው የሚል ጨርሶ አድሃሪ የሆነ አቋም ወስዳችሁ መጋለጥ ይኖርባችኋል። ነው ወይስ አቋማችሁ ይህ ይሆን? እስቲ አንባቢ ይህንን የጠላቶች ዝርዝር እንደገና ይመልከተውና እኛ የታዘብነውን ሌላ ጉድ ይታዘብ

በመጀመሪያ ደረጃ የዚህ መንግስታቸው አይነተኛ ተቃዋሚ ደርጉ መሆኑን ይነግሩናል። ታዲያ በዚህ የሚያሲዩን ምንድነው በዚህ ቅደም ተከተላቸው የሚያምኑልን ይህ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስታቸው በመጀመሪያ ደረጃ ፀረደርግ መፈክር መሆኑን ነው። በዚህ ጥቅሳቸው ከምርጫ የሚወጣው ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ፀረፊውዳልና ፀረኢምፔሪያሊስት መፈክር እንዳልሆነ ማመናቸውን አድርባዮቹ ጨርሶ ልብ አላለም። የኦስፋወሰን/መንገሻ ዲሞክራቲክ ህብረት ንቅናቄ ጊዜያዊ መንግስት የጠየቀው ባስቸኳይ የማይገባውን ስልጣን እጁ ያስገባው፣ አገሪቱን በፋሽስታዊ አመጽ ጨብጦ የያዘውን ፋሽስታዊ ደርግ ለመጣል እንደሆነ በኦክቶበር 8 ቀን መግለጫው አስታውቋል። አድርባዮቹ ደግሞ ይህንን መንግስት የሚጠይቁት ራሱን የቻለ የመንግስት ስርአት ሳይሆን እየተጠናከረ የሚሄደውን ወታደራዊ የፋሽስት መንግስት በአጭር

ለመቅጨት እንደሆነ ሲያስታውቁን ቀጥታ ከሞናርኪስቶቹና ከነሲአይኤ ጋር መቆማቸውን አልተረዱት እንደሆነ በኢትዮጵያ አብዮት፣ በ1968 ዓ.ም. ያለው የመደቦች አሰላለፍ ጨርሶ አልገባቸውም ማለት ነው።

እኛ ግን የዛሬይቱ እቲዮጵያ የመደቦች አሰላለፍ ጠንቅቆ ገብቶናል። ዋና ጠላቶቹን ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ናቸው። የምንታገልለትና የምንሰዋለት ጊዜያዊ መንግስት ቢኖር በነሱ መቃብር ላይ በህዝባዊ አመጽ ተጠንስሶ፣ በህዝባዊ አመጽ ተመርኩዞ የሚገዛው የጭቁን ህዝቦች ፈላጭ ቆረጭ አብዮታዊ መንግስት ብቻ ነው።

ለዚህም የምንከተለውን ጎዳና እብዮቱ እንዲገፋ በሚል ትንተናችን /ስ.ህ.ድ. ቁጥር 25/ ግልጥልጥ አድርገን አሳይተናል። በመጀመሪያ መሬት ላራሹ በሚለው አብዮታዊ መፈክር ስር የተሰለፉት የኢትዮጵያ ገበሬዎች መሬትን እጃቸው ለማስገባት አስፈላጊ ሆኖ ላገኙት ለነፃነታቸው ከፀረህዝብ ሃይሎች ጋር የሞት ወይም የሽረት ትንንቅ በማድረግ ላይ ናቸው። መሬትን እጃቸው ለማስገባት ከፈለጉ በየደረጃው ፖሊሱን፣ ዳኛውን፣ አስተዳዳሪውን፣ ባጭሩ የቀድሞውን ስርአት የመንግስት አውታሮች እየደመሰሱ ስልጣንን እጃቸው ማስገባት እንዳለባቸው ከገዛ እለታዊ ትግላቸው ተምረዋል። ለዚህም ተግባርና መሳፍንቱና ኢምፔሪያሊስቶች ያወጁባቸውን የርስ በርስ ጦርነት ለመመከት አስታጥቁን እያሉ በመጮህ ላይ ናቸው። ፀረዲሞክራቲኩ የደርግ አገዛዝ ማስታጠቅ ማጫረስ ነው። በሚል ፈሊጥ የህዝቡን ጥያቄ አፍኖ ለመያዝ በመሞከሩ ድሃ ገበሬዎችን ዘማቾችን ተራማጅ የመሬት ይዞታ ወኪሎችን በማስጨረስ ላይ ይገኛል።

ነገር ግን ይህ የጭቁኖች እሮሮ አለተሰማምና አብዮታችንን ከመገስገስ፣ ጭቁኖችን ለማሸነፍ የሚያግዳቸው ከእንግዲህ ምንም አይነት ሃይል የለም። የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች ባላቸው አቅም፣ እስከፀጉራቸው የታጠቁትን አድሃሪዎች አመጽ እየመከቱ ከፍተኛ ትምህርት በመቅሰም ላይ ናቸው። ከራሳቸው ሌላ የሚተማመኑበት ምንም ሃይል እንደሌለ ገብቷቸዋል። ስለዚህም በዚህ በያዙት አብዮታዊ ትንንቅ ገፍተው፣ ድርጅቶቻቸውንም አጠንክረው የሚያስፈልጋቸውንም ትጥቅ ከደርጉም ሆነ ከደርጉ ውጭ ፈልገው በአብዮታዊ አመጽ የመንግስትን ስልጣን እጃቸው ያስገባሉ።

እንኳን የትጥቁን ነገር አንስተን ይቅርና፣ ድርጅቶቻቸውን እንኳን ያጠናክሩ ስንል አሁን ካሉትና በአጭር ጊዜ ሊቋቋሙ ከሚችሉት ድርጅቶች በአስቸኳይ እንመራረጥ እያላችሁ ለምትለፍፉት አድርባዮች ይህ ጎዳና ረዥምም ይመስላችሁ ይሆናል። ግን ለአብዮታዊ አዋጅ ቢወጣ ስራ ላይ ይውላል ማለት አይደለም። ስራ ላይ የመዋሉ ጉዳይ ፊውዳሊዝምን፣ ኢምፔሪያሊዝምንና ከነሱም ጋር በዚህ የጥቅም ክሮች የተሳሰረውን የአስተዳደር አውታር በጭቁን ህዝቦች አመጽ በየመንደሩና በየስርቻው መደምሰስን ይጠይቃል። እነዚህ ፀረህዝቦች እስካልተደመሰሱ ድረስ በዲምክራሲያዊ ምርጫ ወኪሎቻችሁን ምረጡና ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት አቋቁመን በመንደራችሁ መደምሰስ ያቃታችሁን አወናባጆች ከእንግዲህ አያዳምጡአቸው። የኢትዮጵያ ጭቁኖች በመንደራቸው ጣፊያ እየተነሱ፣

ከአዲስ አበባ ታናሽና ታላቅ ሰደድልን ብለው ወኪል የሚልኩበት ምንም ምክንያት የላቸውም።

ሁኔታው እንደዚህ ሁኖ ሳለ፣ የመታጠቅና በአብዮታዊ አመጽ ፀረህዝቦችን ደምስሶ አብዮታዊ መንግስትን የማቋቋሙ ተግባር ከፊታችን ተደቅኖ ስለ የታጠቀ አድኃሪያዎችና ፖሊሶች በድሃው ገበሬ፣ በዘማቹ በተራማጁ ላይ መረን ተለቅቀው እንዳበደ ውሻ በሚናከሱበት በአሁኑ ጊዜ ይህንን አንገብጋቢውን የትጥቅ ጉዳይ ችላ ብላችሁ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት የሚለውን አድሃሪ መፈክር በአንቀልባ አዝላችሁ ማላዘን ትችላላችሁ።

እኛ ግን፣ ለኢትዮጵያ ወጣቶቻ ወዝአደሮችና ጭቁን ህዝቦች፣ ያለአንዳች አወደድባይነትና አድርባይነት ተጋድሎአችን የአንድን ህዝብ ነፃነት ለምሳሌ ቁምነገር የማደረግ ታሪካዊ ተጋድሎ በመሆኑ ረዥምና የተወሳሰበ እንደሆነ ያለመታከት እናንገብባለን እስከዚያው ግን አድርባዮችና ኢምፔሪያሊስቶች የሚጠነስሱት ሴራ ተሳክቶ ህዝብም ከትጥቁ ትግል አይኑ ወደምርጫ ተስኖ፣ የናንተን ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ይመርጥላችሁ ይሆናል። ነገር ግን ይህንን ሴራ እንደህዝባዊ ድል ቆጥረንላችሁ፣ የኢትዮጵያ ተራማጆች የትግል ትጥቃችንን አንፈታም። ህዝቡ እንዲደራጅና እንዲታጠቅ የምናደርገውን ቅስቀሳና ትግል ፋታ ስንሰጣችሁ እንቀጥለዋለን። የምትጭኑብንን ዲሞክራሲያዊ መንግስታችሁን በአብዬታዊ ህዝባዊ አመጽ ተቋቁመን፣ የኢትዮጵያን ጭቁን ህዝቦች ፈላጭ ቆራጭና አብዮታዊ አገዛዝ በህዝብ ጠላቶች መቃብር ላይ እንመሰርታለን። አድሃሪዎችም አደርባዮችም ለዚህ ጥርጥር አይግባችሁ።

በመጨረሻ ላይ ለአንባቢዎቻችን ልናስገነዝብ የምንፈልገው አንድ ነገር አለ። የሰፊው ህዝብ ድምጽ የጊዜው ዋና ጠላቶች ፊውዳሊዝም፣ ቢሮክራሲያዊ ካታሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም እንደሆኑና ዋናውም ቅራኔ በነዚህና በኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ መካከል እንደሆነ አመልክቶአል። በዚህ ዋና ጠላቶች ላይ የሚነሱ ሀይሎች በሙሉ በትግል ሊተባበሩ እንደሚችሉና መተባበር እንዳለባቸው ያምናል። የተራማጆችም ተግባር እርስ በራሳቸው መነካከስ ሳይሆን እነዚህን ዋና ጠላቶች በተባበረ ሃይል ለመደምሰስ ሰፊውን ህዝብ ማደራጀትና ማዘጋጀት እንደሆነ ግልጽ ነው። ለመተባበርና የትግል አንድነት ለመመስረት ግን ውዥንብርን አስወግዶ የተጣራ የፖለቲካ መስመር መቀየስ እጅግ አስፈላጊ ነው። ውዥንብር ነዥዎችንም ማጋለጥና መጋገል የሚያስፈልገው ለዚሁ ነው። በዲሞክራሲ ላይም እንደሚያደርጉት ተራማጆችን ለመከፋፈል፣ የህዝቡን ትግል ለማዳከም፣ ተራማጆችን በስም እየጠሩ ለጠላት አሳልፎ ለመስጠት ሳይሆን በዲሞክራሲያ ውስጥም ሆነ ከዚያ ውጭ ካሉት ሃቀኛ ተራማጆች ጋር የትግል አንድነት ለመመስረት ነው። ዛሬ ይህን ብናደርግ ወደፊት በሂደቱ ላይ ለሚፈጠረው ተጨማሪ ችግር ተጠያቂዎች መሆናችን አይቀርም። ዛሬ ይህን ባናደርግ ወደፊት በአብዮቱ ላይ ለሚፈጠረው ተጨማሪ ችግር ተጠያቂዎች መሆናችን አይቀርም። በዲሞክራሲያ ውስጥ ያሉ ሃቀኛ ተራማጆች ጋዜጣቸው የሚነዛውን ውዥንብር ማስወገድ አለባቸው። አበዮታዊ ግዴታቸው ነው።

አድሃሪዎችም፣ አድርባዮችም በህዝባዊ አመጽ ይወድማሉ
የኢዮጵያ ጭቁን ህዝቦች ያሸንፋሉ።

አላማችን የተወሰነ በመሆኑ ብዙ ቅጂዎችን
አላስራጨንምና በይዘቱ የምትስማሙ አንባብያን
በሙሉ አንብባችሁ ላላነበቡ ብታስተላልፉ፣
ከተቻለም ጋዜጣው የሚበራከትበትን ዘዴ
በየፊናችሁ ብትፈልጉ ለትግላችን ይበጃል።